# መስሎ መታየት

ብዙ የሰው ልጆች የተካኑት መላ
ሊ.ቃውንቶች መስለው መታየት በሌላ
ራሳቸውንና ሰውን ሲያታልሉ
ጠምጥመው፣ አጊጠው፣ አለን! አለን! ሲሉ
አዋቂ ከመሆን መምሰል ነው ቀላሉ...
በእንስሳትና ጥቃቅን ፍጥረት
አደገኛ መስሎ ለማስፈራራት
እጅግ ጠቃሚ ነው መስሎ መታየት፡፡
ግን ጠላት ጨክኖ የመጣ ዕለት
መስሎ የቆመ ሰው ወዮው! ውዮውለት!

**ገ/ኢ. ጐርፉ፡፡**